# አቶ ብሩንም ገደሉት!

ነጻነት ዘገዬ

ከጥቂት ሣምንታት በፊት ዶክተር እሌኒ ስለምትባል ወጣት ኢትዮጵያዊ ምሁር - ሲያቀብጠኝ - በእንግሊዝ አፍ ጽፌ በላክሁት ጦማር ሳቢያ በደረሰብኝ የሞራል ውድቀት ላለፉት ብዙ ጊዜያት አንገቴን ደፍቼ ምንም ሳልል ቆይቻለሁ:: አሁን ግን «እስከመቼ ኩርፊያ?» ብዬ ተደፋፈርኩና ብዕሬን አነሳሁ:: የሚገርመው የት ጠፋ ብሎ አንድም ሰው አልጠየቀኝም:: እንዴህ ነን እንዴ ለካ? ትዝብት ነው ትርፉ!

የጠቀስኩላችሁን ጽሑፍ ልኬ በድረ ገፆች መውጣቱን በጉጉት ስጠባበቅ ከአንዱ በስተቀር በሌሎቹ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ:: አቡጊዳ ድረ ገፅ አንጀቴ ውስጥ ገብቶ የተጎዘጎዘው ያኔ ነበር:: በችግርህ ጊዜ የደረሰልህ ሰው እውነተኛ ወዳጅህ ነው የሚባለው ታዲያ ለዚህ አይደል? በዚያ የድረ ገፆች «አድማ» ዙሪያ በወቅቱ ልጫጭር አሰብኩና ኩርፊያየ በረድ እስኪል ልቆይ ብዬ በይደር አዘገየሁት - ሁኔታው ግን ሆድ ሆዴን እየበላውና አካሄዳችን እንዲህ ከሆነ «መዛለቂያችን እንዴት ሊሆን ይሆን?» በሚል እያሰላሰልኩ ነበር ክራሞቴን::

እውነቴን ነው የምላችሁ - ያን ጽሑፍ ደግሜ ደጋግሜ ደገጋግሜ ባነበውም ምንም ስህተት የሚባል ነገር ላገኝበት አልተቻለኝም - እንደአካሄድ:: ችግሩን እንዲነግሩኝም የማውቃቸውን ሰዎች ጠያየቅሁ - ወሃ የሚያነሳ ምላሽ ባላገኝም:: ዶክተሯ የወያኔ ደጋፊ እንደሆነች ሰማሁ - ጥሩ ነው፤ መደገፍም ሆነ መወየን መብቷ ነው:: ታዲያ እኔ ያኔ ምን አልኩ? «ጎበዝ» ብዬ ያደነቅሁዋት በወያኔነት ሳይሆን ስለርሱዋ የዘር ሐረግ ከአብዛኛው የኢትዮጵያ ጎሣዎችና ነገዶች መጠላለፍ ወይም መወሳሰብ በሚመለከት ራሱዋ የጻፈችውን በማንበቤና ያን ለመጻፍ አነሳሳት የተባለውን የነገር መነሾ አንዱ ሩቅ ብዕሲ ስለጠቆመኝ ያንን መርዘኛ አካሄድ በመቃወም ነበር:: የኔ የሃሳብ መደላድል የነበረው «ማንም ሰው በዘር ሐረጉ ምክንያት ጥላቻና መገለል አይድረስበት፤ በማንነቱ ምክንያት መድረክ አይነፈገው፤ በዘር ፍጅት ሳይሆን በሃሳብ ፍጭት አንድ የጋራ ማንነትና የጋራ ሀገር

እንመሥርት፤ በስሜትና በአሉቧልታ ከተነዳን መዳረሻችን አያምርም፤ በረባ ባልረባው ሚና እዬለየን ከምንወጋገዝና ከምንለያይ ይልቅ በሚያስማሙን የጋራ ፈትሎች ዙሪያ ተሰባስበን ቢያንስ ዞሮ መግቢያ ሀገር እንዲኖረን እንጣር . . .» አልኩ እንጂ ራሴኑ በወያኔነት እስከሚያስፈርጅ ድረስ ለዶክተሯ ጥብቅና መቆሜን የሚጠቁም አንዳችም ነገር አልጻፍኩም:: አለመጻፌ የሚበጅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጻፍኩ ቢባል እንኳን ባንድ ቀንና ባንድ ቅጽበት በችኮላ በተከናወነ የፍርድ ሂደት በሚሰጥ «ውሳኔ» እኔንም ሆነ ጽሑፌን በወያኔነት መፈረጅ ከማንም አይጠበቅም:: በዚህ ዓይነት ጭፍን የሚመስል ጉዞ ደግሞ የትም አይደረስም::

በአቡጊዳ በወጣው ያ ጽሑፍ ግርጌ ከተሰጡት ጥቂት የማይባሉ አስተያቶች - የወያኔነትን ሹመት ባገኘሁበት ጽሑፍ ማለት ነው - እንደተረዳሁት ይህች ልጅ በውጭ ከሚኖረው የሀገራችን ሕዝብ ብዙም ፍቅርና ውዴታ ያላት አይመስልም፤ ዳፋዋ ለኔም በመድረሱ ብቻ ሳይሆን ከአስተያየት ሰጪዎች መራር አነጋገር የተረዳሁት ዶክተሪቱ ለገበሬው በ«ማሰብ» ባቋቋመችው የንግድ ልውውጥ አውታር ሳቢያ ከወያኔ ጋር እንደተዛመደችና ያም ዝምድናዋ ከብዙ ሀገር ወዳድ ነን ከሚሉ ዜጎች ጋር ያቆራረጣት መሆኑን ነው:: ቢሆንም የኔ ጽሑፍ ከሥራዋ ጋር አንዳችም ግንኙነት የለውም፤ ወያኔ ሊያስብለኝም አይችልም:: ወያኔማ ብሆን በማን ዕድሌ? እዚህ እናንተ ጋ አታካራ ውስጥስ ምን ይዶለኝ ነበር? መጣጥፉን ደግሞ በማንበብ እውነቱን መገንዘብ ይቻላል::

ወደተነሣሁበት ጉዳይ ከመግባቴ በፊት ግን አንዲት አጭር መልዕክት እንዳስተላልፍ ይፈቀድልኝ:: ወያኔን ላለመሆን በጣም እንጠንቀቅ:: ለፍርድ አንቸኩል:: ለፍርድ ከቸኮልን ብዙ የምናስቀይማቸውና በጎ ፈቃዳቸውን የምናበላሽባቸው፣ ጠንካራ ኅብረት ከሚፈልገው ሀገራዊ ትግልም የምናርቃቸው ዜጎች እየተበራከቱ ይሄዳሉ:: ለሀገር ነጻነት የሚደረግ ትግል እንደጨረባ ተዝካር በሆይ ሆይታና ባልሠከነ የዛር መንፈስ ዓይነት ግልብ የትግል ወኔ በመመራት አይደለም:: ማስተዋልንና ከጥላቻ ፈጽሞ መራቅን ያጠይቃል:: እንደዘመነ ክርስቶስ «ስቅሎ ስቅሎ» ዓይነት የአፍርሳታ ዘይቤ ጎጂ ነው:: አመክዮና ተጠየቅ እውናዊ መርሆዎቻችን ካልሆኑ ታጥቦ ጭቃ መሆን ይከተላል:: ውሳኔን በይደር ማስቀመጡ

ክፋት የለውም። ሀበሻ አንድን ነገር በሞቅታ መወሰን ጉዳት ያለው መሆኑን ለማሳሰብ « ይህን ነገር በውሃ ቀን ብናየውስ?» የሚለው ለበጎ ነው። የመደበኛ ፍርድ ቤቶች የፍርድ ሂደት ዓመታትን የሚወስደውም በቅጽበታዊ ችኩል ብያኔ ፍርደ ገምድልነት እንዳይከሰትና የሰው ሕይወት አላግባብና በከንቱ እንዳይጠፋ ነው። አሁን ከማያቸው አንዳንድ ሁኔታዎች እንደምረዳው እኛ ኢትዮጵያውያን ማስተካከል የሚገባን በርካታ ነገሮች አሉ - ትግላችን እንዲሠምርና በቶሎ ነጻነታችንን እንድንጎናጸፍ ከፈለግን ማለት ነው። የትግሉ ሜዳ በቅጡ ካልጸዳ የመከራ አረንቋ ውስጥ እንደተዘፈቅን እንኖራታለን እንጂ ነጻነት ብሎ ነገር ሱሚ ነው - አትገኝም። በቀላሉ መኮራረፍ ይቅር - ምናባቱና! መቻቻል በመካከላችን ይንገሥ። ስንታረቅም ከአንጀትና ከልብ ይሁን። ነግ ተነግ ወዲያ ወይም ሲያሻትም አሁንና ከአሁን በኋላ ባለ አንዳች ቅጽበት ለምትቀር ዓለም ብለን ከወንድምና ከእህቶቻችን ጋር ቂም በቀልና ጎሚ አንያያዝ። ሃይማኖት ይኑረን - የፈለገውን ዓይነት ይሁን ሃይማኖቱ፤ ብቻ ይኑረን። አንድ ሰው ኅሊናውን ወይም የሃይማኖቱ ቀኖና የሚያዘውን የመልካም ሥነ ምግባር ሕግጋትን ካልፈራ በዓለም ላይ የመጨረሻው ጨካኝ አውሬ መሆኑን አንዘንጋ። እነመለስ ዜናዊ ሀገርን ከነሕዝቡዋ እስከመሸጥ በደረሰ ጭካኔ የተሞሉት ሃይማኖትና ኅሊና ብሎ ነገር ስላልፈጠረባቸው ነው። ሆዳቸውና የሥልጣን አራራቸው ከንዋይ ፍቅራቸው ጋር ተደማምሮ ከሰውነት ተራ አወጣቸውና ይሄውና እንደአንበሣ በብረት አጥር ተከርችመው - ያው ኖሩ መባላቸው እንደሆነ አይቀርም - «እየኖሩ» ነው። ከነሱ ብዙ መማር ይጠበቅብናል። ውስጣችንን እንመርምር። ለአንድ ዓላማ ተሠልፈናል የምንል ወገኖች በርግጥ በአንድ ልብ ነወይ የምንንቀሳቀሰው? በከንቱ የምንወራረፍ አለን ወይ? ትግላችንን በ«አንተ ትብስ፤ አንቺ ትብሽ» የፍቅርና የመተሳሰብ ስሜት ነው የምናካሂደው ወይንስ ልክ እንደወያኔዎቹ በ«ሲለዩ ቡጭቅ» ጅባዊና ዓሣማዊ የእንስሳት ፍልስፍና ነው? የወያኔዎች የርስ በርስ «ፍቅር» ሥልታዊ እንጂ እውናዊ ሊሆን አይችልም - ሆዳም ፍቅር አያውቅምና - ጅብም።

ድረ ገፆቻችንን በሚመለከት ብዙ የምለው ነበረኝ - ግን ለዛሬ ይቅርብኝ። ዋናው ግን ፍቅር ይኑራችሁ፤ መጽሐፉ እንደሚያዝዘው ርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። ለመዋደድ ዕድል ባታገኙ እንኳዋ በከንቱ አትወነጃጀሉ፤ አትካሰሱ፤ አትጠላለፉ፤

ይቅርም ተባባሉ:: አንዳችሁ የአንዳችሁን ውድቀት አትመኙ:: ላንድ ዓላማ የቆመ አካል - ሠርጎ ገብ ካልሆነ በስተቀር - ርስ በርሱ አይነቋቆርም:: መጽሐፉ «የተከፋፈለች መንግሥት አትጸናም» እንዲል ተከፋፍላችሁ ይቅርና አንድ ሆናችሁም የሚጠብቃችሁ ትግል ከባድና ውስብስብ መሆኑን ተረዱ:: ዙሪያ ገባችሁን በአስተውሎት ማትሩ፤ ውስጣችሁን መርምሩ፤ በንጹሕ የኢትዮጵያዊነት ጸበል አካባቢያችሁንና ቤታችሁን ጥመቁ - ያኔ የሚያጋጭ የሚያናጭ ፀላኤ ሠናያት ከአጠገባችሁ ተስፈንጥሮ ወደመጣበት ወደጎሬው ይመለሳል:: ፍቅር ባለበት ጠብ የለም:: ፍቅር ባለበት ክፋትና ተንኮል የሉም:: ፍቅር ባለበት መተሳሰብና መተዛዘን ይነግሣሉ፤ ግጭት፣ ሁከትና አምባጓሮ ለሠላማዊ ኅላዌ ቦታ ይለቃሉ:: ያኔ በታናናሽ መቼቶች የተጀመረው ሠላማዊ ኑባሬ ያድግና ሀገራዊና ብሔራዊ ግዘፍ አግኝቶ የአንድ ሕዝብና የአንድ ሀገር የኅልውና ማረጋገጫ ዋስትና ይሆናል:: የሁላችንም ምኞት ይሄና ይሄም ብቻ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ:: የአጥፊዎች ግን ሥሪታቸው ሌላ ስለሆነ የፍቅርና የሠላም ነገር ሲነሳ ያንዘረዝራቸዋል፤ የውስጥ ሠላምም ይነሳቸዋል እንጂ አይወዱም - ግን የራሳቸው ጉዳይ - ስለነሱ እኛን ምን አስጨነቀን?

አቶ ብሩንም ገደሉት - ገባሁ ወደዋናው ርዕሴ:: ሰሞኑን አንድ ሊትር ቤንዚን ብር 14.87 መሆኑን ሰማችሁ አይደል? ለ15 ብር 0.13 ሣንቲም ፈሪ መሆኑ ነው:: ይገርማል:: ከ0.40 ሣንቲም ገደማ ተነስቶ እዚህ መድረሱ በጣም የሚደንቅ ነው:: ብራችን ጭራሹን ሞቶ ሊቀበር በጣት የሚቆጠሩ ሐሙሶች ብቻ ቀርተውታል:: በዩወሩና በዩሳምንቱ ወያኔ እየተነሳ በነዳጁና በሌላውም የአገልግሎትና የሸቀጦች ዋጋ ላይ አዳዲስ ዋጋ ይቆልላል:: ጭማሬው ግን ወገቡን የሚያጎብጠው ደሞዝተኛ ውን እንጂ ነጋዴውንና ጉቦኛውን አይደለም:: ምንም ዓይነት የዋጋ ጭማሪ ይደረግ ቀጥተኛ ተጎጂው በንጹሕ ደመወዙ የሚተዳደረው ምሥኪን ሠራተኛ ነው:: ነጋዴው ጭማሬውን በቀጥታ ለደንበኞቹ ነው የሚያስተላልፈው - እሱ በምን ዕዳው የምንዱብ ሠራተኛውን ዕዳ ይጋራ? ማንስ ጠይቆት? «የአህያ ባል ከጅብ አያስጥል» እንዲሉ ሆኖብን የዘጠና ሰባቱ ቅንጅት እግዜር ይይለትና ላያዛልቀን የቆሰቆሰው እሳት ባመጣው የቂም በቀል ቁርሾ ይሄውና እየተቃጠልን እንገኛለን - አመክሮ የሌለው የገሃነም እሳት:: በገሃነም እንኳዋን እሁድ እሁድ ያርፋሉ ይባላል:: እኛ ግን

በጭራሽ ዕረፍት ብሎ ነገር አይፈቀድልንም፡፡ የኛ ግዴታ መቃጠል - የወያኔ የማያቋርጥ ተግባር የእቶኑ እሳት እንደፋመ እንዲኖርና እኛን እንዲፈጅ ፍልጥ ሊያውም የደሬና የወይራ ፍልጥ መማገድ ነው - በቃ፡፡ እሳቱ ጋብ የማለት ዝንባሌ ካሳዩ ወዲያው ወዲያው ይቆሰቁስበታል፡፡ ለምን? እኛ ማረፍ የለብንማ! ብናርፍስ? ብናርፍማ ስለሀገር፣ ስለመንግሥት፣ ስለ ድሎትና ምቾት፣ ስለዴሞክራሲ፣ ስለሀገር መቆራረጥና ሳያስማሙ መሸጥ፣ ስለድንበር፣ ስለወደብ፣ ስለመጥፎ አስተዳደር፣ . . . ማሰብ እንጀመርና ሽፍጠኛውንና የመከራ አምባሳደሩን የወያኔ መንግሥት ኅልውና ሥጋት ላይ እንጥላለና! ስለዚህ? ስለዚህማ ሕዝቡ ሁልጊዜ እንዲጨነቅ፣ ከዕለት ጉርስና ከዓመት ልብስ ባልዘለለ የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ተዘፍቆ በኤሎሄ እንዲማስን ፣ ልጆቹን ማሳደግና በወግ አስተምሮ ለቁም ነገር ማብቃት እንዲችል ሳይሆን እየወለደ ለጎዳና ሕይወት እንዲዳርግ. . .  ማድረግ ወያኔዎቹ ሆን ብለው የተጠመዱበት  ዋነኛ ሥራ ሆነ፡፡

የነዳጅ ዋጋ ጭማሬ የማይነካው የኢኮኖሚና የሕይወት ዘርፍ የለም፡፡ አንዳንድ ሞኝ ዜጋ « እሰይ! እንኳዋን ጨመረ! ባለመኪኖቹ ናቸው የሚጎዱት፤ እኔ እንደሆንኩ መኪና የለኝ. . .» ሊል ይችላል - የሚልም ሞልቷል፡፡ ይህን መሳዩ ሰው ግን በርግጥም የዋህ ነው - እልፍ ሲልም ቡልሃ፡፡ ይህን የምላችሁ ከሜዳ ተነስቼ እንዳልሆነ ተገንዘቡልኝ - በርግጠንነት እንዲህ የሚሉ ብዙ ጊዜ ስላጋጠሙኝና እኔም ራሴ የእነሱን መሳሳት ለማሳመን በስብከት ስለደከምኩበትም ጭምር ነው፡፡ የነዳጅ ጭማሬ እንዲያውም ከባለመኪናዎች ይልቅ ይበልጥ የሚጎዳው መኪና የሌላቸውን ነው፡፡ እህል ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባው በምንድነው? ሰው የሚጓጓዘው በምንድነው? . . . እናም ነዳጅ ጨመረ ማለት በሁሉም ዓይነት የንግድ እንቅስቃሴ ላይ የሁሉም ነገር ዋጋ አሻቀበ ማለት ነው፡፡ ታዲያንም በውጭ ያላችሁ ወገኖችችን እባካችሁን ይህንን የወያኔ ግፍና በደል ተረድታችሁ ለሌላው ዓለም አሳውቁልን፡፡ ብራችን በወያኔ ወደር የሌለው ብልሹ አስተዳደር ምክንያት ጋሸቦ የመግዛት አቅሙ ተንኮታኩቷል፡፡ አንድ ሽህ ብር ይዘህ ገበያ ትወጣና የረባ ነገር ሳትገዛበት የት እንደገባ እንኳዋን ሳታውቀው የጠፋ ያህል ይሰማሃል ኘ ቁጭ ብለህ በርጋታ ያወጣሃውን ስታሰላው ግን እንዳልጠፋብህ ትገነዘባለህ፡፡ የ«ያ ሁሉ ገንዘቤ የት ገባ?»ና «የት ጥየው እሆን?» ጥያቄዎችህ ግን

በአዕምሮህ እየተምሰለሰሉ ከአንተው ጋር ቤትህ ድረስ ይጓዛሉ፤ ሲመሽም እንቅልፍ አያስወስዱህ:: በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀርመንን እንደገጠማት ወይም በቅርቡ ዚምባብዌንና ሌሎች የአፍሪካና የኤዥያ ሀገራትን እንደገጠማቸው ያለ የገንዘብ ግሽበት ሊገጥመን ተቃርበናል:: በድሃውና በሀብታሙ መካከል የሚታየው ቅጥ ያጣ ልዩነት ደግሞ ይሰቀጥጣል:: በአንድ በኩል ድሃው ከጥቂት እህል ጋር አስፈጭቶ የልጆቹን ወስፋት ሊሸነግል በከብት ፋርሽካ መሽጫ ሥፍራዎች ተሠልፎ ፋርሽካ ሊገዛ ወረፋውን ሲጠባበቅ ታያላችሁ - በሌላ በኩል ሀብታሙ በሁሉም ኪሱ ረብጣ ብር ይዞ በየሣምንቱ ላንጋኖ ሶደሬና አውሮፓና አሜሪካ ለሽርሽር ሲመላለስ ልትታዘቡ፤ አንድ ቀን አብራው ላደረች ሴትም አቶዝ የምትባለዋን ወይም ሌላ አውቶሞቢል ገዝቶ ሲሰጥ ልታዩ ትችላላችሁ፤ ይህም አይድነቃችሁ - ምክንያቱም ንግዱ በምንም ዓይነት ሕግ በማይገዛ የውንብድና ዘረፋ የከበረ ኢትዮጵያዊ ሀብታም ስለሆነ:: ነገረ ሥራችን ሁሉ እንዳይሆን እንዳይሆን ነው ኀበዝ:: የሃይቲው ቁጣ ወደኛም እንዳያዘግም ሥጋት አለኝ - ሥጋቴ ከሥጋት ተራ አይውጣ እንጂ:: በየሌሊት ክበባቱ የሚሠራው የሶዶምና ገሞራ ዓይነቱ ውቂ ደብልቂ ደግሞ እዚህ ላይ አይነሳም:: የየዝጉብኙ የሽማግሎቹና የአዛውንቶቹ ቅብጠትም እንዲሁ እዚህ ሊነሣ አይሞከርም:: የዋጋ መናር እነዚህን የጥፋት መስኮች አያካትትም::

በአሁኑ ወቅት የሁሉም ነገር ዋጋ ሰማይን አልፎኣል:: በአግባቡ መኖር የሚችሉት ሙሰኞችና ነጋዴዎች ብቻ ናቸው:: ተራ ደመወዝ ከወር ወር መድረስ ካቃታት ዓመታት ተቆጠሩ:: አብዛኛው ዜጋ የሚኖረው በኪነ ጥበቡ ነው:: ልመና በሁሉም ዘንድ እየተስፋፋ ነው:: እንዲያውም መንግሥት በዚህ ሴክተር ላይ ቀረጥ እንዳይጥል ሌላ ሥጋት ተደቅኖብናል ሲሉ ሰምቻለሁ- የኔ ቢጤዎች:: ብዙዉ ዜጋ ደግሞ ዕድሜ ለዲያስፖረው ከዉጭ ሀገር ወዳጆችና ዘመድ አዝማዶች በሚወረውሩለት ወቅታዊም ይሁን ወርሃዊ ምንዳ ይተዳደራል:: በሀገራችን መንግሥት የሚባል ነገር ያለም አይመስልም:: ወያኔ ከማይማን ጀሌዎቹ ጋር በየቀበሌው በስብሰባና በግምገማ ከመንጫጫት በስተቀር ለሕዝቡ እያደረገው ያለ ተጨባጭ ነገር የለም:: እርግጥ ነው መንገዶችና ሕንጻዎች እዚህም እዚያም እየተሠሩ ናቸው:: ሆኖም የሕዝቡን የረሃብ ችግር ከመቅረፍ አኳዋያ የሚፈይዱት

ነገር የለም - ለጥቂት ሀብታሞች የኩራት ምንጭና የኑሮ መሠረት ከመሆን ውጪ፡፡

የመንገዶቹ ነገር ከተነሣ ምንም እንኳዋን የመንገዶች ሥራ በየቦታው ቢታይም የመኪና ፍሰቱን ስናይ ችግሩ ሊቃለል አልቻለም፡፡ ከአራት ሚሊዮን በላይ መኪኖች የሚርመሰመሱባት የቻይናዋ ዋና መዲና ሻንጋይ ውስጥ የጎላ ችግር ሳይታይ ከ300ሺ እምብዝም ያልዘለለ የመኪና ቁጥር ባሉዋት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ግን የሁለትና ሦስት ኪሎ ሜትር መንገድ ለመጓዝ ሰዓታትን መፍጀቱ የወያኔው መንግሥት የሚኩራራበትን ያህል መንገዶች ተስፋፍተዋል ማለት እንደማይቻል ያስገነዝበናል፡፡ በየሥፍራው ተገትረን ነው የምንውል፡፡ የእሳትም ሆነ ሌላ ሀገራዊ አደጋ ቢደርስ ፈጥነን የመድረስና የመከላከል ወይም አደጋን የከፋ ጉዳት ሳያስከትል የመቀልበስ ዕድል የለንም፡፡ በጥቅሉ ያገራችን ችግር እንዲህ እንደዋዛ በአንድ ቁጭታ ተነቦ ማለቅ በሚጠበቅበት መጣጥፍ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ስለዚህ በዚሁ ልሰናበትና ወደየሥራችን እንሂድ፡፡ ቻው፡፡